



ፓና ግእዝ ወቅኔን ሳነባትና ስመረምራት ልቡናየ መልካም ነገርን አፈለቀ ተብለው በመንፈስቅዱስ ገላጭነት ከተጻፉት የግእዝና የንባብ መጻሕፍት ተርታ ተመድባ የግእዝ በሩዋን አስፍታ፣ የእውቀት ወንበሯን ዘርግታ ትልቁንም ትንሹንም አስቀምጣ ንባብ ድግስን የምትጋብዝ ሁና አግኝቻታለሁ። ትውልዱንና ዘመኑንም የዋጀች ድንቅ መጽሐፍ ናት። ለወንድማችን ይህችን መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሳሳ መንፈስቅዱስ የተለያዩ መጻሕፍትን ለመጻፍ ያነሳሳልን እያልሁ፤ አንባብያንም ብዙ የምታተርፉባት ናትና እንድታነቧት ጋብዣችኋለሁ።

መ/ር ሥነፀሐይ ካሴ
የሐዲሳት እና የቅኔ መምህር

ፓና ግእዝ ወቅኔ የልሒቃኑ የነየኔታ መጽሐፍ ብቻ አይደለም፤ የግእዝ ቋንቋን እንደቋንቋ ማወቅ የሚሻ የማንኛውም፣ የማንኛዋም ደቂቅ ጭምር እንጂ። በተለይም ደራሲው በሁሉም የእውቀት ደረጃ ላይ የሚገኝ አንባቢ በቀላሉ ተረድቶ የቋንቋው ተናጋሪ ብቻ ሳይሆን የቋንቋው አመሰጣሪ ለመሆን እንዲችል የተጠበበት መንገድ መጽሐፉን ተመራጭ ያደርገዋል። በተጨማሪም ዘመናዊ ትምህርት ቀመስ ለሆኑና ለግእዝ ቋንቋ እምብዛም ቀረቤታ ለሌላቸው አንባብያን የቋንቋ መሠረታውያንን በእንግሊዝኛውም ጭምር ባካተተ መልኩ መቅረቡ ያልተለመደና የሚበረታታ ተግባር ነው። ደራሲ ዲ/ን ይኸነው ብዕርህ ይለምልም እያልኩ በቀጣይ ሥራም እንደምትገለጥ ተሥፋዬ የጸና ነው።

ዲ/ን ኤፍሬም አብርሃም (ዶ/ር)
በጎንደር ዩኒቨርሲቲ መምህርና የ"ዴጋኒ" መጽሐፍ ደራሲ

የመጽሐፉን ይዘት ለማሳየት ያህል። ከታች ቀርቧል፤ ይጠቅማችኋል ብየ አስቤአለሁ እስኪ እዩት።

አኩቴት

በመጀመሪያ ፓና-ጥበብ ወአእምሮ እግዘአብሔር ሆይ ጀምሬ እንድጨርስ ስለረዳኸኝ ክብር ምስጋና ይድረስኽ።

...

መ/ር ፍሬ-ሕይወት አረጌ (የቅኔ መምህር እና የዐቢየእግዚእ ወኪዳነምሕረት (የአለቃ ወልደአብ) የመጻሕፍት ትርጓሜ ጉባኤ ቤት ምስክር መምህር) ከዘመናችን ቁርሎሶች አንዱ፣ እንደከዋክብት የበዙ በቅኔው የተራቀቁ ሊቃውንትን በማፍራት ላይ ያሉት መ/ር ኤርምያስ ሞላ (የሐዲሳት እና የቅኔ መምህር)፣ ድሎት እና ቅንጦትን ስለቤተክርስቲያን እና ተማሪዎችዎ የሰውት መ/ር ሥነ-ፀሐይ ካሴ (የሐዲሳት እና የቅኔ መምህር)፣ ስለመጽሐፉ ቅርጽ አስተያየትዎን የሰጡኝ የ"ስደተኛው ታቦት" እና "በቅኔያችን ሲቃኝ ዘመናችን" ደራሲ ቆሞስ አባ እንድርያስ አምባቸው (በደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ መምህር እና Phd Candidate)፣ አባዬ (መ/ር አለማየሁ ይደግ) እና ላላዬ (ወ/መድኅን ጸጋየ) ዘራዕያነ-ግእዝ በልበ-ኩሉ አው ጥንቱን የምናይባችሁ መስታውቶች፤ ከፊደል ተነስቶ በብሂል አልፎ በምስጢር ላይ በመፍሰስ የተደመደመዉ የማስተካከያ እና የአስተያየት ጅረታችሁን ምስጋና ብቻ የማይገልጠው ቢሆንም ውለታችሁን እግዚአብሔር ይመልስ እያልኩ ከልብ የመነጨ ምስጋናየን አቀርባለሁ።

...

በመጨረሻ ነገር ግን ትልቁ ምስጋናየን ለደብረ-ልዑላን ድልአምባ ቅዱስ አማኑኤል ወአቡነ አረጋዊ ሰበካ ጉባኤ እና ማኅበረ ካህናት፣ ለሉማሜ ሰንበት ትምህርት ቤት እና ማኅበረ ቅዱሳን እንዲሁም ለፋሲል ግቢ ጉባኤ እያቀረብሁ ትጋታችሁን አሁንም እንድትቀጥሉ በሚል የልጅ ማሳሰቢያ ጭምር ላቅ ያለ ምስጋናየን አቀረብሁ።

የአዘጋጁ መገኛ

ኢሜይል: yihenewandualem20@gmail.com

ስልክ: 0949961420

Facebook: Yihenew Andu

ተጨማሪ መገኛ፡ በሐራ ዘኢትዮጵያ ትምህርት ቤት የግእዝ መምህር

ጎንደር

መጽሐፉን ማንበብ ያለበት ማን ነው?

1ኛ) ግእዝ ቋንቋን ማወቅ እና ማውራት የሚፈልግ ሁሉ፤

2ኛ) ግእዝ ቋንቋን የሚማሩ ከዐጸደ ህፃናት እስከ ዩኒቨርሲቲ ያሉ ተማሪዎች፤

3ኛ) በየትኛውም ሰአት የሚደረግ ቅኔን መረዳት የሚፈልግ ሁሉ፤

4ኛ) ቅኔ መመርር የሚፈልጉ እና የጀመሩ ተማሪዎች፤

ማውጫ

አኩቴት.....2

መግቢያ 8

ምዕራፍ አሐዱ .....

፩. በግእዝ ለማውራት የሚረዱን ቃላት..... 9

፩.፩ አስተአምሮ ርእስ (ራስን ማስተዋወቅ) (Self Introduce)

፩.፫ ዜና-መጥቅዕ (የስልክ ወሬ) (Telephoning).....

፩.፬ አብሾዎች (ምዕላዳት).....

፩.፭ ክፍላተ ሕዋስ (የአካል ክፍሎች) (Body Parts).....

፩.፮ ሰብአ ቤት (ቤተ ሰብ) (Family Members) .....

፩.፯ እንስሳት ዘቤት (የቤት እንስሳት) (Domestic Animals).....

፩.፰ እንስሳተ-ገዳም (የዱር እንስሳት) (Wild Animals).....

፩.፱ ሑለ-ቤት ወአልባስ (የቤት እቃ እና ልብሶች) (Furnitures and Clothes)

፩.፲ ሑለ-ቀትል (የጦር እቃዎች) (Weapons).....

፩.፲፩ ሕብራተ-ምግብ (የምግብ ዓይነቶች) (Types of Food)

፩.፲፪ ሕብራተ-ስቴ (የመጠጥ ዓይነቶች) (Types of Drink).....

፩.፲፫ ሕብረ-እክል (የእህል ዓይነት) (Type of Grain) .....

፩.፲፬ አገባባት (መስተዋድዶች) (Prepositions).....

፩.፲፬.፩ የሚዘረዘሩ አገባባት.....

፩.፲፭ አውስኦተ-ቃል (ቃለ ምልልስ) (Conversation) .....

ምዕራፍ ክልኤቱ.....

፪. መራሕያን.....

፪.፩ አስሩ መራሕያን.....

፪.፩.፩ የመራሕያን ባለቤትነት (Subjective Pronouns) .....

፪.፩.፪ ማሰሪያ አንቀጽ መሆን (ነባር አንቀጽ) (የመሆን ግስ) (Verb to be)

፪.፩.፫ ቅጽል (Adjective) ወይም የስም ገላጭ ሲሆኑ.....

፪.፪ አገናዛቢ መራሕያን (Possesive Adjective) .....

፪.፪.፩ ሳይናበብ ሰዋስውን ገንዘብ (የራስ) ማድረግ.....

፪.፫ ተሳቢ መራሕያን (Objective Pronouns) .....

፪.፬ ባለቤት መራሕያን (Subjective pronouns) .....

ምዕራፍ ሠለስቱ .....

፫. በግእዝ ውስጥ የሚገኙ ቃላት .....

፫.፩ ሰባቱ የግእዝ ፊደላት .....

፫.፪ አንቀጽ እና ዓይነቶቹ (Verb and Its Type)

፫.፫ ገቢር ተገብሮ (ተሳቢ ባለቤት) .....

፫.፫.፩ የሰዋስው ገቢር (የስም ገቢር) .....

፫.፫.፫ የግስ (አንቀጽ) ገቢር እና ተገብሮ .....

፫.፬ ማናበብ /በማናበብ ገንዘብ ማደራረግ /Making Possessive

፫.፭ አምስቱ አዕማደ አርእስት .....

፫.፮ አራቱ አሥራው ፊደላት እና አመላቸው

፫.፯ ቅጽል እና ዓይነቶቹ (Adjective and Its Type)

፫.፰ ዘር እና አይነቶቹ .....

፫.፱ አገባብ .....

፫.፲ ነባር .....

፫.፲፩ መሳግር .....

፫.፲፪ ሠራዊት 13

፫.፲፫ ምዕላድ እና አይነቶቹ .....

ምዕራፍ አርባዕቱ .....

፬. ቅኔ .....

፬.፪ ወርቅ ሰም እና ሕብር .....

፬.፫ ወርቅ ወደ ቅኔ ሲቀየር .....

፬.፬ ቀለም አቆጣጠር .....

፬.፭ የንባብ ዓይነቶች እና የቅኔ ዜማ ልክ .....

፬.፭.፩ የስም አነሳስ ሕግ .....

፬.፮ የቅኔ ሙያ (የዓ.ነገር ሙያ) .....

፬.፮.፩ አገባባት (መስተዋድዶች) (Preposotions) እና ሙያቸው

ምዕራፍ ኃምስቱ .....

፫. ቀለምን ማርዘም እና ማሳጠር .....
፫.፩ ለመሳብ የፈለግነውን በተሳቢ መሳብ .....
፫.፫ በቂ ማድረግ .....
፫.፬ የውእቱን ፍች ማስመርመር (ውእቱን ማውጣት) .....
፫.፭ ቅጽል በተዛራፊ መካከል ማስገባት .....

፫.፲፬ በውስጥ ማሰሪያ የሚያወጡ አገባባትን መጠቀም .....
፫.፲፭ ምስክር መጠቀም .....

ምዕራፍ ስድስቱ .....
፮. የቅኔ ብልሽት (የዓ.ነገር ስሕተት) .....
፮.፩ አጎላማሽን ከተጎላማሽ ማራራቅ .....
፮.፪ ለገቢር ተገብሮን መቀጸል ወይም ለተገብሮ ገቢርን መቀጸል (መመሰል) .....

፮.፪.፪ ለተገብሮ “ገቢር” ሲቀጸል .....
፮.፭ ከትእዛዝ፣ ከዘንድ እና ከቦዝ አንቀጽ ሁሉንም አገባባት መጣል .....
፮.፭.፫ "ውእቱ"ን ሲመረምሩ እና ዐቢይ አገባብ ሲወድቅባቸው .....
፮.፮ ዘርፍን ገቢር ማድረግ .....

፮.፲፩ በር ከፋች ይዘው የሚወድቁትን ያለ በር ከፋች መጣል .....

፮.፲፪ ቅጽልን ከአገባብ እና ተዛራፊ አሳልፎ መቀጸል .....
፮.፲፪.፪ ተዛራፊን ማሳለፍ .....
፮.፲፩ በምሳሌ መካከል ወይም በቅጽል እና ባለቤት መካከል አንቀጽ ማስገባት ...
፮.፲፯ ሁለተኛውን ንዑስ አንቀጽ ሳያዘረዝሩ ሳያዛርፉ መጠቀም
፮.፳ ቦዝ አንቀጽን እና ንዑስ አንቀጽን ሳይዘረዝሩ የዘረዘሩ አድርጎ መጠቀም .....

፮.፳፫ ደካማ ቅጽሎችን አሳልፎ መቀጸል
፮.፳፭ ንዑስ አንቀጽን አገባብ ወድቆበት ወይም ዘርፍ ይዞ ከፊት ማሳብ .....
፮.፳፯ ይቤን ማስጠቅጠቅ .....
፮.፳፰ ሰሚን በመሀል ማምጣት .....

ምዕራፍ ሰብዓቱ .....
፯. አናቅጽን ማርባት .....
፯.፩ አናቅጽን ለማርባት የምንጠቀምባቸው ሕጎች

፮.፭.፭ የግስ አርእስት ከነትርጉማቸው .....
፮.፪ ሲገሰሱ ፊደል የሚቀይሩ እና የሚጎርዱ ግሶች.....

፮.፪.፪ (ሀ፣ሐ፣ኀ እና አ፣ዐ)፣ ወ እና የ በቀደሰ ቤት
፮.፪.፫ (ሀ፣ ሐ፣ ኀ እና አ፣ ዐ)፣ ወ እና የ በተንበለ ቤት
፮.፪.፬ በ “ተ” የተነሱ ግሶች.....

፮.፬ ሲዘረዝሩ አዲስ ባሕርይ የሚያመጡ ግሶች .....
፮.፭ አእመረ እና ምልክቱ.....

ምዕራፍ ሰመንቱ.....
፯. ግስ ከሀ እስከ ፐ .....

ምዕራፍ ተስዓቱ.....
፱. ጉልቄ-ግእዝ (የግእዝ ቁጥር).....
፱.፭ ከአስር እስከ መቶ ያሉ ቁጥሮች.....
፱.፭ ከአንድ ሚሊየን እስከ መቶ ሚልየን (ትእልፊት)

ዋቢ መጻሕፍት.....200

መግቢያ

ግእዝ እንደ ቋንቋ ሲታይ በጥንትነትም ይሁን በአ<u>ለ</u>ው የቃላት ብዛት እና ለዓለም የሚጥቅሙ ምስጢራትን ሰንዶ በመያዝ በቀዳሚነት የሚጠቀስ ቋንቋ ነው። ምዕራባውያንም በዩኒቨርሲቲያቸው (University) እስከ ሦስተኛ ድግሪ ይማሩታል። ለምን? እኛ ሀገር ግን ...። የታሪክ መጽሐፋችንም ከሞቱ ቋንቋዎች (ትንሽ ተናጋሪ ያላቸው) መድቦት እናገኘዋለን። ስለሆነም የዚህ ዘመን ትውልድ Geez (ግእዝ) ተናጋሪ የለውም ያለውን ታሪክ ማስቀየር የሚችለው መቼ ነው? ይልቁንም በግእዝ ወደተሰነዱት ሰነዶች እና ሲቆጥሩትም ይሁን ሲያደርጉት መ<u>ላ</u> አካልን ሰ<u>ቅ</u>ዞ ወደሚይዘው የቅኔ ምርምር ሁሉም ሰው መግባት የሚጀምረው መቼ ነው? እኔም ቅኔን ለመማር ስጀምር የነበረው የመምህራን እና የእኔ ድካም፤ መቼ ይሆን ቀለል የሚል? የሚሉት ጥያቄዎችን መመለስ የዚህ መጽሐፍ ምክንያተ-ጽሕፈት ነው።

ፓና የግእዝ ቃል ሲሆን መብራት ማለት ነው። መብራት ሲበራ ጨለማ ይርቃል። ይህ መጽሐፍ ቢነበብም የእውቀት ጨለማ ይርቃልና፤ መጽሐፉ ፓና ግእዝ ወቅኔ ተብሎ ተሰይሟል። የመጽሐፉ ዓላማ በዋናነት፡-

፩. ግእዝን ማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ፣ መማር ለጀመሩ ተማሪዎች እና እያስተማሩ ያሉ መምህራንን ድካም ቀለል አድርጎ ማቅረብ እና ቢያንስ ሌላው ቢቀር ማንኛውም ሰው አማርኛ ቅኔዎችን መረዳት እንዲችል ማድረግ፤

፪. አንድ ተማሪ ቅኔ ቤት ሂዶም ይሁን ባለበት ቅኔን ሲማር ወይም ዓ.ነገር ሲሰራ ብዙ የሚያስረዳው ሰው ያስፈልገዋል። እርሱ የነገረው ቅኔ ወይም የሰ<u>ራ</u>ው ዓ.ነገር ስሕተት መሆን አለመሆኑንም ለማወቅ ብዙ መድከም ይጠበቅበታል፤ ይህን መቀነስ

መጽሐፉ በአጠቃላይ ዘጠኝ ምዕራፎችን በመያዝ በየቀኑ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸውን ቃላት፣ መራሕያንን እና ዓይነቶቹን እስከ አገልግሎታቸው፣ የቅኔ እና ሰምና ወርቅ ትርጉም፣ የፊደላት (ቀለም) አቆጣጠር ሙያ እና ዜማ ልክ፣ ዓ.ነገር ወይም ቅኔን ለማርዘም ወይም ለማሳጠር ስለሚረዱን ጉዳዮች፣ በዓ.ነገር ወይም ቅኔ ውስጥ ሲገኙ ስሕተት ስለሚሆኑ ብሂሎች፣ ግስ ወይም አንቀጽ ከጎላፊ እስከ ዘር እንዴት እንደሚገሰስ እና ሌሎችን ግሶች ለመግሰስ የሚያገለግለን አእመረ ከነምልክቱ፣ ከሀ እስከ ፐ ያሉት ግሶች ገቢር ወይም ተገብሮ መሆናቸውን በማመልከት እስከ አርእስታቸው በመያዝ በመጨረሻም ግእዝ ቁጥር እንዴት እንደሚሰራ እየተነተነ ስለቅጽል አንስቶ ያገባድዳል። መጽሐፉ አንዳንድ ሥርዐተ ነጥቦችን ከአገልግሎታቸው ውጭ ለመለያነት ብቻ ተጠቅሞ ታገኛለህ። በዋናነት ለቋንቋውም ይሁን ለቅኔው ጀማሪ የሆኑትን ታሳቢ ተድርጎ ስለተጻፈ የበለጠ ለማቅለል ሲባል አንዳንድ እንግሊዝኛ ቃላት በአማራጭነት ቀርበዋል። በእንግሊዝኛ እንደ አማራጭ ቀረበ ማለት ግን እንግሊዝኛውን ስላልተረዳኸው የሚቀርብህ ምስጢር አለ ማለት አይደለም። በመጽሐፉ ውስጥ ደ**መ**ቅ (**Bold** text) ተደርገው የተጻፉት አብሮ ካለው ቃል ለ<u>የ</u>ት እንዲሉ ወይም ስለእነርሱ ስለሚያወራ ትኩረት እንዲ<u>ሰ</u>ጣቸው የሚፈልጉ ፊደላት ወይም ቃላት ናቸው። እንደብዙዎቹ መጻሕፍት የወንድ አንቀጽን ተጠቅሟል። ይህም አድርጊ አድርግ አድርጉ እያለ አንባቢን እንዳያሰለች ሲሆን ስለአንድ ጉዳይ እየተነተነ ሌላ ጉዳይ ቢነሳበት ይህን ያለበትን ገጽ ለማመልከት ተሞክሯል። የተለያየ አጻጻፍ ያላቸውን እና ማብራሪያ የሚፈልጉ ጉዳዮችን በግርጌ ጽሑፍ (Footnote) ያብራራል። አንባቢያን ሆይ! የነደለውን ሞልታችሁ የጠ<u>መ</u>መውን አቅንታችሁ እንድታነቡት እየተማጸንኩ እግዚአብሔር እንደፈቀደ ወደፊት ሰፋ ባለመንገድ የማቀርበው ይሆናል።

መልካም ንባብ!!!

፩. በግእዝ ለማውራት የሚረዱን ቃላት

እንኳን በደና መጣህ ወዳጄ! ወዳጄ አንባቢ መግቢያየን አንብበሀል? ሥርዐተ ነጥብ አጠቃቀሜንስ?

አንተ ሰው! መራሕያንን፣ ስምንቱ የግስ አርእስትን (የግስ አለቆችን) እስከ አረባባቸው፣ መጠይቃዊ ቃላትን እና አብዝኆ ቃላትን እንዲሁም በመጠን ያልበዙ ግሶችን እና ነባሮችን ብትይዝ በግእዝ ለማውራት ብዙ አትቸገርም፤ የግእዝ ጽሑፎችንም በቀላሉ ትረዳለህ። …

፩.፩ መጠይቃዊ ቃላት (መጠየቂያ ቃላት) (Interrogative Words)

…

መኑ=ማን	መኑ ስምከ? =ስምህ ማነው?/ ማነው? ስምህ፣ **መነ** ጸዋዕከ? =ማንን ጠራህ? “**ነ**” የሆነ ተሳቢ ስለሆነ ነው
እለመኑ=እነማን	እለመኑ መጽኡ? =እነማን መጡ? እለ ትርጉሙ **እነ** ማለት ነው።
አይ=የቱ	አይ ውእቱ ርቱዕ? = ትክክል የቱ ነው?/ የቱ ነው? ትክክል
አያት=የቶች	አያት ውእቱ አዝማደ-ሙሴ? = የቶች ናቸው? የሙሴ ዘመዶች/ የሙሴ ዘመዶች የቶች ናቸው?
ምንት=ምን	ምንት ተፈጥረ? =ምን ተፈጠረ?፣ ምን**ተ** ኀሠሥከ? =ምን ፈለክ?/ምንን ፈለክ
ምንታት=ምኖች	ምንታት ተፈጥሩ? ምኖች ተፈጠሩ?
ስፍን=ስንት	ስፍን ተሰይጠ? =ስንት ተሸጠ?፣ ስፍን ተገዝአ? =ስንት ተገዛ፣ስፍነ አውጽአ? =ስንት አወጣ?

…

፩.፰ እንስሳተ-ገዳም (የዱር እንስሳት) (Wild Animals)

አንበሳ=አንበሳ	ወይጠል=ድኩላ (ፌቆ)	ደኅብያ=ኩብኩባ/አንበጣ
ትንንያ =ትንኝ	ከራማልዮ=አሳማ	ሐራውያ=ከርከሮ
ሆባይ=ዝንጀሮ	ቁንቁኔ=ነቀዝ	ዓሣ=ዓሣ
ቶብኒ=ትኋን	ቆብኒ=ቅማል	ሐለስትዮ=ጦጣ
አቅራብ=ጊንጥ	ዝእብ=ጅብ	ቁንጽል=ቀበሮ
ሀየል=ዋለያ	አድገ መረብ=የሜዳ አህያ	ዖፍ=ወፍ
ነምር=ነብር	አናምርት=ነብሮች	አርዌ=አራዊት
ቆቅህ=ወንድ ቆቅ	ጡራይካ=ሴት ቆቅ	ቀይዘል=ሚዳቋ

....

፩.፲፬ አገባባት (መስተዋድዶች) (Prepositions)

አገባብ እና ትርጉም	**ምሳሌ (ምስክር)**
ዲበ፣ ላዕለ፣ መልዕልተ=በ..ላይ	ዲበምድር= በምድር ላይ፣ላዕለደብር=በተራራ ላይ
ውስተ=በ..ውስጥ	ውስተቤት=በቤትውስጥ፣ ውስተጎልጎታ=በጎልጎታ
ስለ= ***"ሰለ" ሰለሚሆኑ አገባባት በገጽ 99 ላይ በዝርዝር ታገኛለህ***	
ከመ=እንደ	ከመሖረ=እንደሄደ፣ ከመየሐውር=እንደሚሄድ ከመእዝራ=እንደ እዝራ
እም (እምነ)=ከ	እምነያሬድ=ከያሬድ፣ እምትቅትል=ከምትገድል
በ=በ	በልገት=በጎጆ
መንገለ፣ ኀበ፣ ውስተ፣ ለ፣ ዘ፣ እንተ፣ እም=ወደ	ተመይጠ ለብሔረ-ግብጽ= ወደግብጽ አገር ተመለሰ፣ ዐርገ ዘሰማይ=ወደሰማይ ወጣ
ለ=ለ	ለእዝራ ይከውን=ለእዝራ ይሆናል
ቅድመ=ከ..ፊት=	ቅድመእዝራ=ከእዝራ ፊት
ማዕከለ=መካከል	ማዕከለሙሴ ወአሮን=በሙሴ እና አሮን መካከል
ድኅረ=ከ..ኋላ	ድኅረመጽአ=ከመጣ በኋላ፣ድኅረቤቱ=ከቤቱ በኋላ

....

የመራሕያን አገልሎት

፪.፩.፪ ማሰሪያ አንቀጽ መሆን (ነባር አንቀጽ) (የመሆን ግስ) (Verb to be)

ሁለተኛዉ የመራሕያን አገልግሎት ማሰሪያ አንቀጽ መሆን ነው። Verb to be i.e am=ነኝ፣ is=ነው/ናት፣ are=ነህ/ነሽ/ናችሁ። ነባር የተባሉበት ምክንያት ሳይገ̲ሰሱ (ሳይረቡ) ቀዳማይ (ሀላፊ)፣ ካልዓይ (ትንቢት) እና ትእዛዝ (ራብዓይ) አንቀጽ ስለሚሰጡ ነው። ማሰሪያ አንቀጽ ሁነው ሲያገለግሉ አንዱ መራሒ ሰባት ትርጉም አለው። የፈለከውን ተጠቀም። አረባባቸው እንደሚከተለው ነው፡-

1. ውእቱ=ነው፣ ኾነ፣ ይኾናል፣ ይኹን፣ ነበረ፣ ይኖራል፣ ይኑር
2. አንተ=ነህ፣ ኾንክ፣ ትኾናለኽ፣ ኹን፣ ነበርክ፣ ትኖራለህ፣ ኑር
3. ውእቶሙ= ናቸው፣ ሆኑ፣ ይሆናሉ፣ ይሁኑ፣ ነበሩ፣ ይኖራሉ፣ ይኑሩ
4. አንትሙ= ናችሁ፣ ሆናችሁ፣ ትሆናላችሁ፣ ነበራችሁ፣ ትኖራላችሁ፣ ኑሩ
5. ....

፫.፩ ሰባቱ የግእዝ ፊደላት

...

ስለሚነሳ ሞክሸ (ተመኩሳይያት) ፊደላትን ማየቱ ጥሩ ነው። ተሞክሳይያት ፊደላት በድምጽ አንድ አይነት በአጻጻፍ እና አገልግሎት የተለያዩ ፊደላት ናቸው። እነዚህም ሀ ሐ ኀ፣ ሠ ሰ፣ አ ዐ እና ጸ ፀ ናቸው።

“ሀ” ሃሌታው ሀ ሲባል **ሃሌ** ስንል የምንጽፍበት ሀ ማለት ነው። **ሐ** ሐመሩ ሐ ስንል **ሐመር** ስንል የምንጽፍበት ሐ፣ **ኀ** ብዙኃኑ ኀ ማለት **ብዙኃን** ስንል የምንጽፍበት ኀ ማለት ነው። **ሠ** ንጉሠ “ሠ” ማለት “ንጉሥ” ስንል የምንጽፍበት ሠ፣ **ሰ** እሳት ስንል የምንጽፍበት ሰ፣ **አ** አልፋ ስንል የምንጽፍበት አ፣ **ዐ** ዐይን ስንል የምንጽፍበት ዐ፣ ጸ ጸሎቱ ጸ ማለት ጸሎት ስንል የምንጽፍበት ጸ፣ **ፀ** ፀሐይ ስንል የምንጽፍበት ፀ።

ሠረቀ^{ቶ}=ወጣ፤ ምሥራቅ=የፀሐይ መውጫ፣ **ሰረቀ**^{ቶ}=ሰ̲ረቀ፤ ሰራቂ=ሌባ በዚህን ያህል ፊደላት የትርጉም ለውጥ አላቸው።

❖ ሁሉም ፊደላት በግእዝ ውስጥ የንባቡን አይነት የመወሰን ድርሻ አላቸው።***ሰለንባብ ኣይነቶች በገጽ 61 ኣይ***

....

አንቀጽ እና ዓይነቶቹ (Verb and Its Type)

... ሲነገሩ አንቀጽ የሚለውን የሚጨምሩ 5 ናቸው...

<u>E.ንኡስ[1] አንቀጽ</u> ንእሰ= አነሰ ካለው ግስ የሚወጣ ሲሆን ትንሽ አንቀጽ ማለት ነው። ውእቱን ካልመረመረ በቀር ማሰሪያ አንቀጽ ስለማይሆን ንኡስ ተብሏል። በአምስቱ አእማድ ስለሚረባ አምስቱም የራሳቸው የሆነ ንኡስ አንቀጽ አላቸው። ይህ አንቀጽ ሁለት አይነት ነው፤ ያለ **ት** እና በ **ት** የሚመሰረት። ሲተረጎም በ **አ** ለጀመረ ግስ **ማ፤** ለሌላው ግስ ደግሞ **መ** ብሎ በማስቀደም ነው (አወቀ= **ማ**ወቅ፣ ሄደ= ***መ***ሄድ፣ መታ= ***መ***ምታት)። ሁለቱን ባሕርያቱን ከታች ተመልከት።

<u>፩. የቀተለ፣ የገብረ እና የከህለ</u> ቤት የ***መጀመሪያው*** ንዑስ ሲመሰረት የተነሳበትን ፊደል **ሳይለውጥ** መካከሉን **ሣልስ** መጨረሻውን ደግሞ **ሳድስ** ያደርጋል። ቀቲል=መግደል፣ ሰኪብ=መተኛት፣ ሰቂል=መስቀል፣ ክሂል=መቻል፣ ገቢር=ማድረግ፣ ስሒክ=መሻከር፣ ስኢን=መድከም፤ ይላል። ይህ የመጀመሪያው ንኡስ አንቀጽ አይዘረዝርም (**ለ** የለውም) ቀቲል፣ ክሂል፣ ባርኮ፣ ሴስዮ፤ **ይላል** እንጅ ቀቲሉ ለምናሴ፣ ሰቢኩ ለዮናስ **አይልም** ነገር ግን ዘር የሌላቸው ግሶች ከሆኑ እና እንደዘር ካገለገለ ይዘረዝራል።

ሁለተኛው ንኡስ አንቀጽ በትርጉም ከመጀመሪያው ንኡስ አንቀጽ ጋር አንድ ሲሆን ግሱ የጨረሰበትን ፊደል **ሰባተኛ** አድርጎ **ት** ን ይጨምራል። ቀተለ=ቀቲሎት፣ ሰከበ=ሰኪቦት፣ ሰቀለ=ሰቂሎት፣ ክህለ=ክሂሎት፣ ገብረ=ገቢሮት፣ ስሕከ=ስሒኮት፣ ስእነ=ስኢኖት። ይላል። ይህ አንቀጽ ካልዘረዘረ ወይም ዘርፍ ካልያዘ ብቻውን አይቆምም (**ዘ** የለውም)። ቀቲሎቱ፣ ሰኪቦቱ፣ ክሂሎቱ፣ ቀቲሎቱ ለምናሴ=የምናሴ መግደል፣ ሰኪቦቱ ...

<u>፫.፫</u> ገቢር ተገብሮ (ተሳቢ ባለቤት)

ገቢር ማለት ‘‘ገብረ’’ አደረገ ካለ ግስ የሚወጣ ንዑስ አንቀጽ ሲሆን ማድረግ ተብሎ በቀጥታ ይተረጎማል። ‘‘ተገብሮ’’ ተገብረ ተደረገ ካለ ግስ ሲነሳ መደረግ ተብሎ ይተረጎማል። ገቢር ተገብሮን የሰዋስው እና የግስ ገቢር ተገብሮ ብለን በሁለት ከፍለን እናየዋለን።

<u>፫.፫.፩</u> የሰዋስው ገቢር (የስም ገቢር)

ሰዋስው ማለት ማሰሪያ አንቀጽ ያልሆነ የማንኛውም ነገር ስም ነው። ምሳሌ፦ መላእክት፣ በግዕ፣ እምረት= ማወቅ፣ ሐዊር= መሄድ፣ ቅዳሴ፣ ድንግል፣ምንዳቤ= ችግር፣ ጎል= በረት፣...

በሰዋስው ጊዜ “ገቢር” በግእዝ፣ በራብዕ፣...

<u>፫.፫.፫</u> የግስ (አንቀጽ) ገቢር እና ተገብሮ

የግስ ገቢር እና ተገብሮ ከሰዋስው ገቢር እና ተገብሮ ይ<u>ለ</u>ያል። የግስ ገቢር ተገብሮ በዋናነት መሳብ (**ሳ** ይላላል) እና አለመሳብን (**ሳ** ይላላል) መሰረት አድርጎ የሚገ<u>ለ</u>ጽ ነው። ...

<u>ገቢር ግስ (Active Verb)</u>፡ ዋና ግስ በመባልም ይጠራል። ይህ ግስ ድርጊት ፈጻሚውን እና ድርጊት ተቀባዩን በአንድ ጊዜ የሚገልጥ ግስ ነው።

---

[1] ኪዳነወልድ ክፍሌ በሁለቱም ተጠቅመው “ንዕሰ=አነሰ”፣ “ንእሰ=አነሰ” ሲሉ መ/ታ ይትባረክ አካሉ “ንዕሰ=አነሰ” ይላሉ። ሊ/ት ያሬድ ሽፈራው ደግሞ “ንእሰ=አነሰ” ብለው ጽፈዋል።

<u>ተገብሮ ግስ (Passive Verb</u>

ተገብሮ ግሶች በዋናነት ከፊታቸው ፊደል **ተ** ን በመጨመር ይመሰረታሉ። ነገር ግን ተለቅሐ= ተበደረ፣ ተመጠወ= ተሰጠ፣ ተጸገወ= ተሰጠ፣ ተወከፈ= ተቀበለ፤ እነዚህን የመሰሉ ግሶች ፊደል **ተ** ን ከገቢር ግሱ በፊት ጨምረው **ገቢር** የሚሆኑ ልዩ ግሶች ናቸው።...

ተ ን ሳይጨምሩ ተገብሮ የሚሆኑ ግሶችን በግስ ዝርዝር ላይ ***በገጽ 137 ሊይ***

አዕማደ አርእስትን በቀላሉ ለመመስረት ይህን ሕግ እንጠቀም።

፩. አድራጊ ግስ ዋና ግስ የሚባለው ነው።ይህን በቃል መያዝ ነው አማራጩ። “+” ይህን ሲደመር ብለህ አንብብ

፪. (ተደራጊ=ተ+አድራጊ) ከአድራጊ ግሱ በፊት **ተ** ብንጨምር ተደራጊን ይሰጠናል።

፫. (አስደራጊ=አ+[6]አድራጊ)

፫.፲፪ ሠራዊት

ሰርዌ ያለው ቃል ሲበዛ ሰራዊት ይላል አማርኛው እና ግእዙ አንድ አይነት ትርጉም አለው። ሰራዊት የሚባሉት ከአርእስት ጋር በፊደል የተለያዩ ነገር ግን...

፬.፪ ወርቅ ሰም እና ሕብር

ወርቅ፡ በሰም ተሸፍኖ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት የሚመለክበት፣ ቅዱሳን የሚወደሱበት፣ ለሰዎች አክብሮታችንን የምንገልጥበት የተደበቀው ክፍል ነው።።

...

ምሳሌ ፯: - በ12 ቀን ስሰራ ‘‘ሙሴ ባሕሩን በበትሩ ከፈለ።’’ ስቀይረው

#ነረምሳ ሙሴ፡የኤርትራ የባሕር መጠንን በበትሩ ለካ።።#

፬.፬ ቀለም አቆጣጠር

...

አንድ ሳድስ ፊደል ብቻውን ሳድስ ባልሆኑ ፊደላት መካከል ከመጣ እንደቀለም **አይቆጠርም**

:- መጽሐፍ 3 ቀለም አለው። በ **“መ”** እና በ **“ሐ”** መካከል የመጣው ፊደል **“ጽ”** ቀለም ሁኖ አይቆጠርም።

የስም አነሳስ ሕግ

ማንኛውም ስም በ**ሳድስ** ካልጨረሰ አይነሳም። ስለዚህ ይነሳል? አይነሳም? የሚለው ጥያቄ መቅረብ ያለበት በሳድስ ከጨረሰ ነው። ጎቡእ ስም፣ ... ገነት ያለው ገነታት ስለሚል፣ ቤተልሔም ተናባቢ ስም ስለሆነ፣ ....

<u>የማይነሱ ስሞች</u>

1ኛ. ሁለት ግእዝ ፊደላት ከሳድሱ በፊት ሲመጡ፡- ፋሲ**ለደስ**፣ እን**በረም**።

2ኛ. ከሳድስ በፊት ካዕብ ፊደል ሲመጣ፡- ኢየ**ሱስ**፣ ፊልከስዩስ።

፬.፭.፩ ጉባኤ ቃና

የመጀመሪያው የቅኔ ክፍል እና ባለ ሁለት ስንኝ ሲሆን በሁለት ይከፈላል። ግእዝ እና እዝል ተብሎ፤ ከጉባኤቃና እስከ ዘአምላኪዬ ድረስ በአጠቃላይ ሁለት ሕጎችን ላለመርሳት ሞክር።

1ኛ ወዳቂ ተቀባይ የለም፤ ማለትም ወዳቂ ተቀባይ አይሆንም

2ኛ ሰያፍ ቤት መምቻ የለም፤ ሰያፍ ቤት መምቻ አይሆንም እኒህን ከጣስን ቅኔው ስሕተት ይሆናል።

ሀ. ግእዝ ጉባኤ ቃና

በአንዱ ቤት 4 በአንዱ ቤት 4 በአጠቃላይ 8 ቃሎች ወይም ሐረጎች አሉት። ...

፬.፭.፪ ዘአምላኪዬ

ከጉባኤ ቃና እና ከሚበዝኑ ውጭ ሁሉም ቅኔዎች ማንደርደሪያ አላቸው።ማንደርደሪያውም ሁለት ዓይነት ነው። ረዥም እና አጭር። በቅኔ ውስጥ የፈለከውን መጠቀም ትችላለህ።

<u>ረዥም ማንደርደሪያ፡-</u> መደብ መጀመሪያዉ ተነሽ ወይም ተጣይ ከ2 እስከ 4፣ ሰያፍ ከ3 እስከ 5፣ ወዳቂ መደብ አይሆንም።

...

እመወጻኤ-ዖቅ አዳም ላእከ-ሃይማኖት ዘዔሰ፤

ኤርምያስ አምላከ-ዚአነ ሥጋ-ያሬድ ለብሰ፤

ወምድረ-ዚአነ ለነ በኪደተ-እግሩ ቀደሰ።

፬.፮ የቅኔ ሙያ (የዓ.ነገር ሙያ)

የቅኔ ሙያ ማለት በአንድ ቅኔ ውስጥ ያሉ ዓ. ነገሮች፣ ቃሎች (ቃላት) ወይም መስተዋድዶች በዚያ ቅኔ ውስጥ ያላቸው ማንነት፣ አማርኛ ፍቺ (ትርጉም) እና በቅኔው ውስጥ ያላቸው ድርሻ ነው።።

ምሳሌ፡-፩ አበበ አንበሳ ገደለ **ወይም** (አበበ አንበሳን ገደለ) የዚህን ዓ.ነገር ሙያ ስንሰጥ

፡-፡- አበበ=ባለቤት (ድርጊት ፈጻሚ) (Doar of the ation)

፡-፡- አንበሳ=ተሳቢ (ድርጊት ተቀባይ) (Receiver of the action)

፡-፡- ገደለ=ማሠሪያ አንቀጽ (አንበሳን የሚስብ) (አንበሳን ተሳቢ ያደረገ) (Verb)

…

- ቤተ-መጽሐፍ==የመጽሐፍ ቤት
- ዘመጽሐፍ ቤት==የመጽሐፍ ቤት
- ቤት ዘመጽሐፍ==የመጽሐፍ ቤት

ወ	ም	ውጥን ጨራሽ	በልዐ ኀብስተ ወጼተሎ= እንጀራ በላ ጠጅም ጠጣ
ወ	ፈጽሞ	ጀምላይ	ተሰብአ ወተሰገወ=ፈጽሞ ሰው ሆነ
ወ	ላ	ማንጸሪያ	ብእሲ ይትሌቃሕ ወኢይፈዲ= ሰው ላይከፍል ይበደራል
ወ	የ	ቅጽል	እስመኀልቀ ኃጥእ ወኢይትሜህር ገቢረ-ጽድቅ= ጽድቅ ማድረግን የማይማር ኃጥእ ጠፍቷልና
እስመ	እኮ	ማሰሪያ አጋዥ	ሄኖክ እስመቆመ= ሄኖክ ቆመእኮ ቆመ ማሰሪያ፣ እስመ ማሠሪያ አጋዥ
ምስለ	ከ…ጋር	አፈቃቃሪ	ምስለሐና=ከሐና ጋር
ምስለ	እንደ	አስፈች	ምስለገብርኤል=እንደገብርኤል
ከመ	እንደ	አስፈች	ከመሊቅ=እንደሊቅ

፮. ቀለምን ማርዘም እና ማሳጠር

፮.፩ ለመሳብ የፈለግነውን በተሳቢ መሳብ

፡- ላእከ አእመረ ምስጢረ= ላእከ አእመረ **በ**ምስጢር= ላእከ አእመረ **ውስተ**ምስጢር= ላእከ አእመረ ላዕለምስጢር= ተማሪ ምስጢርን አወቀ፡፡

፮.፪ የውእቱን ፍች ማስመርመር (ውእቱን ማውጣት)

ውእቱ ማሰሪያ ሲሆን ትርጉሙ “ነው” የሚል ሲሆን ሳይጠራ (በንባብ ሳይኖር) መውጣት ይችላል።

፡- ዘተናገረ ሙሴ= የተናገረ ሙሴ ነው፡፡ **ሙሴ** ውእቱን መርምሮ ማሰሪያ፣ **ዘ** በቂ፣ "ተናገረ" እንዳያስር በቂው ይጠበቀዋል

፡- ያሬድ እንዘይበልዕ= ያሬድ እየበላ ነው፡፡ **ያሬድ** ባለቤት፣ **እንዘ** ውእቱን መርምሮ ማሰሪያ፣ **ይበልዕ** እንዳያስር እንዘ ይጠበቀዋል ….

<u>፮.፫ ማሕፀን ቅጽል ማድረግ፡-</u> ማሕፀን ቅጽል ማለት…

፮. የቅኔ ብልሽት (የሚነገር ስሕተት)

፮.፰ ከትእዛዝ፣ ከዘንድ እና ከቦዝ አንቀጽ ሁሉንም አገባባት መጣል

በእነዚህ አንቀጾች ላይ ውእቱን ካልመረመሩ በቀር አገባብ አይወድቅባቸውም ፡፡ ነገር ግን በቦዝ አንቀጽ “ወ፣ ኢ”፤ በትእዛዝ አንቀጽ "ወ፣ ኢ እና ለ"፤ በዘንድ አንቀጽ "ወ፣ኢ፣ እም፣ ከመ፣ እንበለ እና ቅድመ" ይወድቁባቸዋል።

፡- እስመአእሚሮ=አውቆና፣ እስመያእምር=ያውቅዘንድና፣ እንተእግበር፤ **አይልም**

፮.፰.፩ "ወ፣ ለ፣ ኢ" ከቦዝ ና ከትእዛዝ ሲወድቁ

ቦዝ አንቀጽ በዋናነት ከመጨረሻው ፊደል በፊት ያለውን ፊደል ሣልስ በማድረግ የሚመሰረት ነው። ቀደሰ=ቀዲሶ ***ሰለቦዝ አንቀጽ በገጽ 37 ኣይ***

"ወ" ከቦዝ ሲወድቅ አቀብሎሽሽ ወይም ደጋሚ ይሆናል፤ ከትእዛዝ ሲወድቅ ደግሞ እንደአፈታቱ ይሆናል፡፡

፡-ወሐዊሮ=በሄደ ጊዜ፣ ሄዶ ተብሎ ይተረጎማል፤ የ"ወ" ሙያም አቀብሎ ሸሽ ነው።

፡- ኢተዘኪሮ አበሳነ=በደላችንን ሳያስብ፣ “ኢ” ትርጉሟ “ሳ” ነው።

፮.፰.፪ ዘንድ አንቀጽ "ከመ፣ እንበለ፣ ቅድመ፣ እም"ን ይዞ ዐቢይ አገባብ ሲወድቅበት

እስመእምይብላዕ እመያነብ ይኄይሶ=ከሚበላ ቢያነብ ይሻለዋልና።

- “እም” ከዘንድ አንቀጽ ላይ ወድቆ **ከ** ይሆናል።
- "ከመ፣ ቅድመ፣ እም" ሙያቸው “አውታር በጣሽ” ይባላል።

፮.፳፪ ይቤን ማስጠቅጠቅ

፡- ላእከ ጸመወኒ ይቤ፤ እንዘአሐውር ኀበሐተታ ቤትየ= ተማሪ ወደምርምር ቤቱ ስሄድ ደከመኝ አለ፡፡...

፮.፳፫ ሰሚን በመሀል ማምጣት

ሰሚ የምንላቸው ሆይ የሚል ንባብ ሳይኖር **ሆይ** የሚል ማውጣት የሚችሉትን ነው።

<u>የባለቤት ሰሚ፡-</u> የባለቤት ሰሚ በመጀመርያ ወይም በመጨረሻ በመምጣት ይሰማል። አምላክ ደምከ ውሕዘ በኢይሁድ፣ ወይም ደምከ ውሕዘ በኢይሁድ አምላክ= አምላክ በኢይሁድ ደምህ ፈሰሰ። “ደምከ” የውሕዘ ባለቤት፣ “አምላክ” ባለቤት ሰሚ (ደምከ ያለውን የውሕዘን ባለቤት የሚሰማ)

፡- ለምንት ላእካን ዘይጸልም ገጽከሙ፤ **አይልም**

፯. አናቅጽን ማርባት

፪. ወ በቀደሰ ቤት ባሉ ግሶች

መጀመሪያ ሲመጣ፡- ያለአመል ቀደሰን መስሎ ይረባል። (ወደ̲ሰ ይቄድ̲ስ ይወድ̲ስ ይወድ̲ስ)፣ (ወሠ̲ረ ይቄሥ̲ር ይወሥ̲ር ይወሥ̲ር)

መጨረሻ ሲመጣ፡-

፯.፬ ሲዘረዝሩ አዲስ ባሕርይ የሚያመጡ ግሶች

1/ በ **ቀ**፣ በ **ነ**፣ በ **ከ** እና በ **ገ** የደረሱ (የጨረሱ) ግሶች በቅርብ እርባታ ጊዜ (በቅርብ መራሕያን) በ**ቀዳማይ** አንቀጽ ያ̲ለ ባዕድ ማለትም አ̲ዘርዛሪያቸውን ትተው እራሳቸውን ያጠብቃሉ። **ቀ፣ ከ፣ ገ** (አንተ፣ አንቲ፣ አነ፣ አንትሙ እና አንትን) ባለው ሲነርዱ፤ **ነ** ግን ንሕነ ባለው ብቻ ይነርዳል። የሚነርዱት **በቀዳማይ ብቻ** ነው።

፯.፭ አእመረ እና ምልክቱ

5. ያችን (እርሷን) (ይእቲን) ሩቂቱ ሴትን ሲያውቃት

- **ውእቱ** አእመራ^ወዳ፣ አእመራሃ^ወዳ=እርሱ አወቃት
- የአ̲ምራ^ወዳ፣ የአ̲ምራሃ^ወዳ =ያውቃታል
- ያእምራ̲^ተነ፣ ያእምራሃ^ወዳ=ያውቃት ዘንድ
- ያእምራ̲^ተነ፣ ያእምራሃ^ወዳ=ይወቃት

፷. ግስ ከሀ እስከ ፕ

1. አስተጋብአ^{ባረ}=ሰበሰበ^{ገቢ} የሁ
2. አስተዐ^{ቀተ}=እጅ መንሻ ሰጠ፣ገበረ^{ገቢ}
3. አቅየዐይዐ^{ተን}/አቅያዕይዐ^{ማሕ}=ተፋ፣ተፋፋ^{ገቢ} የመትፋት
4. አብሕአ^{ከሀ}=አቦካ፣አኮመጠጠ^{ገቢ}
5. አንሳዕስዐ^{ማሕ}=አፈላ^{ገቢ}፣አፍለቀለቀ^{ገቢ}፣ገነፈለ^{ተገ}፣ፈላ^{ተገ} ለሚፈላ
6. አንበዐ^{ቀተ}=አለቀሰ^{ተገ} የሁ

አንጉዐ^{ቀተ}=ቀለጠመ፣ሰበረ^{ገቢ}

...

፬. ጐልቄ-ግእዝ (የግእዝ ቁጥር)

- 2=ሁለት=፪=ክልኤቱ
- 3=ሦስት=፫=ሠለስቱ
- 4=አራት=፬=አርባዕቱ
- 5=አምስት=፭=ኀምስቱ

- 11=10+1=፲፩=አስር እና አንድ=ዓሠርቱ ወአሐዱ.... ይህም **ዓሠርቱ** ሲደመር **አሐዱ** ማለት ነው

- 148,619=(14*10,000)+((80+6)*100)+10+9=(፲+፬)*፼)+((፹+፮)*፻)+፲+፱=፲፬፼፮፻፲፱= <u>ዓሠርቱ ወአርባዕቱ እልፍ</u> <u>ሰማንያ ወስድስቱ ምዕት</u> ዓሠርቱ ወተስዓቱ

- 385,864,942=385,000,000+860,000+4900+40+2= (385*100*10,000)+(86*10,000)+(49*100)+40+2= (38,500+86)*10,000+(49*100)+40+2= (30,000+8500+86)*10,000+(49*100)+40+2= <u>ሠለስቱ እልፍ ሰማንያ ወኃምስቱ ምዕት ሰማንያ ወስድስቱ</u> እልፍ አርብዓ ወክልኤቱ

…

<u>የዕለት ቁጥሮች (ቅጽሎች)</u>

1) አሚር (አይቀ<u>ጸ</u>ልም)=አንድ ቀን , እሁድ= አንደኛ
2) ሰኑይ= ሁለተኛ፣ ሁለተኛ ቀን
3) ሠሉስ= ሦስተኛ፣ ሦስተኛ ቀን

…